# Alexandria City Public Schools

## የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት (Family Life Education)፣ 8ተኛ ክፍል ውስጥ

*ዳግም-ምልከታ ለማድረግ ያለ-መብት:* ወላጆች እና አሳዳጊዎች፤ በትምህርት ቤት ክፍሉ/division የሚሰጠውን፤ በፕሮግራሙ ውስጥ ጥቅም-ላይ የሚውለውን የጽሁፍ እና የድምፅ-እይታ (audio-visual) ትምህርትን ቁሳቁሶችን ጨምሮ፤ የ'Family Life Education Program'ን በድጋሚ-የመመልከት መብት አላቸው። ወላጆች እና አሳዳጊዎች፤ ልጃቸውን ከ'Family Life Education' የትምህርት-አሰጣጥ፣ ከሁሉም ወይም ከተወሰነው-ከዚህ ክፍል እንዲወጡ-ፈቃድ እንዲያገኙ የማድረግ መብት-አላቸው።

*የፕሮግራም ግቦች:* የACPS፣ የ'Family Life Education' ስርዓተ-ትምህርት፤ ሁሉን-አቀፍ የሆነ፣ ቅደም-ተከተል ያለው ከK-12 ፕሮግራም ሆኖ፤ በቤተሰብ አኗኗር እና በማህበረሰ ግንኙነቶች ላይ - ለዕድሜያቸው-ተገቢ በሆነ የትምህርት-አሰጣጥን አካትቶ እንዲቀርብ የተቀረጸ ነው። የትምህርት-አሰጣጡ የተቀረጸው፤ ሊኖር-የሚያስፈልገውን የወላጅ ተሳትፎን ለማበረታታት፣ አዎንታዊ የሆነ የራስ-ጽንሰ-ሃሳቦችን ለማሳደግ እና ከእኩዮቻቸው-ጋር እኩል-ሆኖ ለመታየት ሲባል - የሚመጣባቸው ጫና መቋቋሚያ፣ እና እንደ ተማሪዎቹ የዕድገት ደረጃዎች እና አቅሞች መሠረት - በዘመናዊ አኗኗር ውስጥ የሚገጥማቸውን ጫናዎች የሚቋቋሙበትን መንገዶች ማቅረብ ነው።

*የፕሮግራም ቅደም-ተከተል:* በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ (Virginia Department of Education) በታዘዘው-መሠረት፣ በACPS ውስጥ፣ የ'Family Life Education' ስርዓተ-ትምህርት፣ ከK-10ኛ ክፍሎች - በሚከተሉትን የጽንሰ-ሃሳብ ይዘቶች ላይ በStandards of Learning ላይ መሠረት አድርጎ የትምህርት-አሰጣትን ያካትታል:

1. የቤተሰብ አኗኗር እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች፤
2. የቤተሰብ ግንኙነቶች ያላቸው ከፍተኛ-ዋጋ፤
3. የወሲባዊ-እንቅስቃሴዎችን - ወደ ሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ያለው ከፍተኛ ዋጋ፤
4. የመታቀብ ትምህርት፤
5. ለወንዶች፣ ሴቶች፣ ልጆች፣ እና ማህበረሰቦች፤ ጋብቻ ያለውን - ጥቅሞች፣ አስቸጋሪ-ፈታኝ ነገሮች፣ ኃላፊነቶች እና ያለውን ከፍተኛ ዋጋ፤
6. የሰው-ልጅ ወሲባዊ-መለያ (Human sexuality)፤
7. የሰው-ልጅ መራባት/መዋለድ (Human reproduction)፤
8. ያልታሰበ እርግዝና በሚፈጠር ጊዜ፤ ለማደጎ-የመስጠትን አዎንታዊ የሆነ አማራጭ - ያለው ጥቅሞች፤
9. በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች፣ መንስዔ፣ መከላከያ፣ እና የሚያመጡት ችግሮች፤
10. የሰውን-ልጅ ከቦታ-ቦታ ያለፈቃድ ዝውውር (human trafficking)ን መከላከል፤
11. የፍቅር-ጓደኝነት ጥሰት (dating violence) - በዚህ ውስጥ መካተት ያለበት፤ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ማንኛውም የወሲብ ክንውን ከማድረጋቸው በፊት ስምምነት መስጠት፣ ጥቃት-ያለባቸውን የግንኙነት ፀባዮችን ማወቅ፣ የወሲብ ጥቃትን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎችን፣ ሊገኙ-የሚችሉትን የማማከር እና ሕጋዊ የመረጃ-ምንጮችን ማወቅ፣ እና፣ የወሲብ-ጥቃት በሚከሰት ጊዜ - ወዲያውኑ የሕክምና ትኩረት እና ምክርን ማግኘት ጠቃሚነትን፣ እንዲሁም የሕግን አስፈላጊነት፤ እንዲያውቁ ማድረግን ያካትታል፤ እና
12. የአዕምሮ ጤና ትምህርት እና ግንዛቤ።

*የስርዓተ-ትምህርት መስመሮች (Strands):* ስርዓተ-ትምህርቱ፤ በሦስት የመለኪያ ርዕሶች (measurement topics) ዙሪያ የተገነባ - ይህም ጭብጥ-ያለው መስመር (thematic strands)፣ እና የሂደት መደበኛዎች - ግንዛቤዎችን ዘላቂ በማድረግ እና መሠረታዊነት ያላቸውን ሂደቶች በፕሮግራሞ መሃከል-ላይ በማድረግ ላይ ትኩረት አድርጎ-የተገነባ ነው።

1. መስመር-ማስመር (Draw the Line)/የተሰመረውን መስመር ማክበር
2. የእርስ-በርስ ግንኙነቶች (Relationships)
3. ተፅዕኖዎችን መተንተን

ለእያንዳንዱ ክፍል - ከእነዚህ የመለኪያ ርዕሶች (measurement topics) ጋር ጎን-ለጎን በማድረግ፤ ግቦችን ማስተላለፍ እና የክንውን-ሂደቶችን ይገመግማል።

*ስርዓተ-ትምህርትን ለአንዳፍታ-በምልከታ-ላይ:* በ8ኛ ክፍል የ‘FLE’ የትምህርት አሰጣጡ ወቅት፤ የሚከተሉት ርዕሶች ላይ - ምላሽ-ተሰጥቶባቸዋል።

# የ8ኛ ክፍል - የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት

**ክፍል/Unit 1:** **መስመር-ማስመር (Draw the Line)/የተሰመረውን መስመር ማክበር**

በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች በወሲባዊ-እንቅስቃሴ ውስጥ የመሳትፍን አደገኛ-ሁኔታዎች - እና እነዚህን አደጋዎች እንዴት ማስወገድ ወይም መቀነስ እንደሚችሉ ምልከታ ያደርጋሉ። በዚህ ክፍል/unit፣ የኮንዶም-አጠቃቀም (condom demonstration) ተካትቷል። ተማሪዎች፤ ለአደገኛ-ሁኔታዎች እና ወሲባዊ ግንኙነቶች - “እምቢ/no” የሚሉባቸውን ስልቶችንም ልምምድ የሚያደርጉ ይሆናል። ተማሪዎች ባላቸው-ገደቦች ላይ ጠንክረው የመቆየት ልምምድን - ሚናን በመጫወት ይጠቀማሉ።

1. **ትምህርት/Lesson 1፡ HIV እና ወጣቶች (Teens) – ከHIV ጋር መኖር የሚያመጣውን ተጽዕኖ ማወቅ እና፣ ተማሪዎች እራሳቸውን ከHIV፣ ሌሎች ‘STDs’፣ እና ካልተፈለገ-እርግዝና እንዴት መስመሩን-ስምረው ላለማለፍ እራሳቸውን የሚጠብቁበትን የግል-ቃል መግባትን እንደሚያደርጉ መምራት።**
2. **ትምህርት/Lesson 2፡ መስመሩን-ገድቦ የማስመር (Draw the Line) እራስን-መፈተኛ/Challenge – ‘HIV’ ሰውነትን እንዴት እንደሚያውክ፣ እና እንዴት እንደሚተላለፍ እና እንደማይተላለፍ መወያየት።** በተጨማሪም፤ ሌሎች ‘STDs’ ያላቸውን የተለመዱ-ምልክቶች ላይ መወያየት እና፣ መታቀብን እንደ የመከላከያ ተመራጭ-መንገድ በማድረግ መለየት።
3. **ትምህርት/Lesson 3፡ አስቸጋሪ የሆኑ ጊዜያት (Difficult Moments) – ገደቡን ጠብቆ ለመቆየት አስቸጋሪ ሊሆን የሚችሉ ሁኔታዎችን መፈተሽ፣ የወሲብ ስሜቶች ሊገቱ እንደሚችሉ መገንዘብ፣ ለተማሪ የየግል-ሁኔታዎች - የትኛው ሁኔታዎች የበለጠ-አስቸጋሪ እንደሚሆኑ አጉልቶ-መመልከት።**
4. **ትምህርት/Lesson 4፡ ገደብ-ባደረጋችሁት ነገር ላይ ሙጥኝ-ብሎ መቆየት (Sticking to Your Limit) – አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ጥቅም-ላይ ሊውሉ የሚያስችሉ ስልቶችን በዝርዝር-መግለጽ፣ መስመራቸውን ጠብቆ የመቆያ ችሎታዎችን ላይ በመነጋገር መፈተሽ።**
5. **ትምህርት/Lesson 5: ‘HIV’ ካለው ሰው ጋር መነጋገር –** ተጋባዥ ተናጋሪ-እንግዳ (Guest speaker) በማድረግ
6. **ትምህርት/Lesson 6፡ ሊደርስባችሁ-የሚችለውን አደጋ መቀነስ (Reduce Your Risk) – ለ‘HIV’፣ ‘STDs’፣ እና እርግዝና አደጋዎችን ለመቀነስ - በውጤታማነታቸው መሠረት የመከላከያ ዘዴዎችን መደልደል፤ የኮንዶም አጠቃቀም ላይ - ማድረግ ያለባችሁን፣ እና “ማድረግ የሌለባችሁን (dos and don’ts)” ማወቅ፤ መታቀብን መምረጥ - ተመራጭ-የሆነ የመከላከያ መንገድ እንደሆነ እውቅና-መስጠት።**
7. **ትምህርት/Lesson 7፡ ደህንነትን-ጠብቆ መቆየት (Staying Safe) – መስመሩን-ሊያልፍ የሚችል የሚመስሉ ሁኔታዎችን በአ ዕምሮ ምስልን-ቀርጾ የመመልከት መሳሪያን በመፍጠር መለየት፤ እና መስመሩን-ላለማለፍ የግላችሁ የሆነውን በጣም አስፈላጊ-የሆነውን ምክንያት ማስታወስ።**

**መደበኛ-ደረጃ ያለው መማር (Standards of Learning):**
8.7, 8.10, 8.11, 8.14

<table>
<tr>
<td></td>
<td>
<u>ክፍል/Unit 2:</u> የእርስ-በርስ ግንኙነቶች (Relationships)<br><br>
በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ ተማሪዎች - በጉምስና ጊዜያቸው ወቅት - ስላላቸው የፍቅር-ግንኙነት (dating) ምንነት ያስረዳሉ። በጤናማ ግንኙነት ውስጥ ተመራጭ-በሆኑት ባህሪያቶች ላይ፣ ተማሪዎች ይወያያሉ። በፍቅር-ግንኙነት (dating) ውስጥ እያሉ፣ ስለ ዲጂታል እና ማህበራዊ ሚድያ (Social Media) ደህንነት ላይ ይወያያሉ። ተማሪዎች፤ ጤናማ-ያልሆነ እና መርዛማ-የሆነ ግንኙነት ባህሪያቶችን በመግለጽ-ይወያያሉ። ተማሪዎች፤ ጥቃትን እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንደሚችሉ፣ እና ወሲባዊ ጥቃት (sexual abuse) እና የፍቅር-ጓደኝነት ጥሰት (dating violence) ምን ዓይነት ሕጋዊ እደምታዎች (legal implications) እንዳላቸው ይመለከታሉ።<br><br>
1. ትምህርት/Lesson 1፡ ጤናማ-የሆኑ ግንኙነቶች (Healthy Relationships) - የጤናማ የሆኑ ግንኙነቶችን - ምርጥ-የሚያደርጋቸውን ነገሮች መለየት፣ የግል-ግንኙነቶችን ማጤን፣ እና በዲጂታል-የፍቅር ጓደኝነት (digital dating) አማካኝነት ሊፈጠሩ-የሚችሉትን አደጋዎች እውቅና-በመስጠጥ - መወያየት።<br>
2. ትምህርት/Lesson 2፡ ጤናማ-ያልሆነ ግንኙነቶች (Toxic Relationships) - ጤናማ-ላልሆነ ግንኙነት ባህሪዎች-ሆነው ሊታዩ የሚችሉትን ነገሮች መለየት እና አለአግባብ-ጉዳት እየደረሰባችሁ ወይም ሌላ ሰው እየደረሰበት ከሆነ እንዴት መርዳት እንደምትችሉ ማወቅ።
</td>
<td>መደበኛ-ደረጃ ያለው መማር (Standards of Learning):<br>8.4, 8.5, 8.13</td>
</tr>
<tr>
<td></td>
<td>
<u>ክፍል/Unit 3:</u> ተፅዕኖዎችን መተንተን<br><br>
በዚህ ክፍል/unit ውስጥ፤ በሚዲያ ውስጥ - ወሲባዊነት ስለአለው መልዕክቶች፣ እና በወጣት-ልጆች ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደሚያደርስ፣ ትንታኔ መስጠታቸውን ይቀጥላሉ። ተማሪዎች፤ የአዕምሮ ጤናቸውን እና በግንኙነቶች (relationships) ላይ ተጽዕኖ ሊያደርሱ ስለሚችሉ ሌሎች ምክንያቶች ላይ - ተጨማሪ ትንታኔንም ያደርጋሉ። እነዚህ ምክንያቶች የሚያካትቱት፤ ጭንቀት፣ ማጣት/loss፣ በወጣት-እርግዝና፣ ዕፆች፣ እና አልኮል-መጠጥ ናቸው። የጭንቀት ምንጭች-ምን እንደሆኑ የሚለዩዋቸው እና የመቋቋሚያ ስልቶችም የሚፈተሹ-ይሆናል።<br><br>
1. ትምህርት/Lesson 1፡ በሚዲያ - ስለፆታዊ ሁኔታዎች የሚተላለፉ መልዕክቶች (Messages About Sexuality in the Media) - ስለ ፆታዊ-ሁኔታ (sexuality) የየግል እሴቶቻችን መለየት፣ ከውጪ የምንጮች-ስለፆታዊ-ሁኔታ (sexuality) በርካታ መልዕክቶችን መለየት፣ እና አንድ-ሰው ስለራሳቸው-ስለፆታዊ-ሁኔታ (sexuality) በሚሰጡ መልዕክቶች እንዴት ተጽዕኖ ሊደርስበት እንደሚችሉ በትንታኔ-መመልከት።<br>
2. ትምህርት/Lesson 2፡ ጭንቀት እና የመቋቋሚያ ስልቶች (Stress and Coping Strategies) - ለጎረምሳ-ልጅ (adolescence) -የጭንቀቱን መንስዔን መለየት፣ ጭንቀትን-ለመቆጣጠር - ጤናማ የሆኑ የመቋቋሚያ ስልቶችን መግለጽ፣ እና ነገሮች-በዝተው በመጨናነቅ-ላይ በሚሆኑ ጊዜ እንዴት እርዳታን ማግኘት እንደሚቻል መገንዘብ።
</td>
<td>መደበኛ-ደረጃ ያለው መማር (Standards of Learning):<br>8.6, 8.8, 8.9, 8.12</td>
</tr>
</table>